# ቁማር

## ወጣ!ገባ!    ቦ ቼ-ቦ ቼ!!!

የሚመኙትን ለማግኘት፣መጣርና ተግቶ መሥራት አይነተኛውና ተገቢው መንገድ ሲሆን ከዚያ ውጭ ሥልጣን ይዞ በመዝረፍና በሙስና መንገዶችም የሚሹትን ሃብትና ንብረት፣ገንዘብ መሰብሰብ ይቻላል፤ከሌብነት ባልተለየም መንገድ ሊዘርፉ የሚችሉበት ሕጋዊና ሕገወጥ መንገድ ተዘርግቷል።

የሎተሪና ካዚኖ በሕጋዊ መንገድ፣በመንግሥት እውቅና ግብር እየከፈሉ የሚንቀሳቀሱ የቁማር የዘረፋ ጨዋታዎች ሲሆኑ ከነዚህ ውጭ ደግሞ በሕገወጥ መንገድ ሕዝብን በማታለልና በማጭበርበር የሚከናወኑ የቁማር ጨዋታዎች አሉ፤ከነዚያም ውስጥ ”ወጣ!ገባ!፣ቦቼ!  ቦቼ!  ” በየመንገዱ ዳር ዱርዬዎች ተሰባስበው አላፊ አግዳሚውን እያነሆለሉ የሚያታልሉበት አንዱ የዘረፋ መንገድ ነው።

ዱሮ የመጀመሪያዎቹ አስራዎቹ ዕድሜዬ አዲስ አበባ በሃብተጊዮርጊስ ድልድይና፣አሜሪካን ቢ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ መንገድ ዳር ከበው ገባ ወጣ!ቦቼ-ቦቼ!  እያሉ ጠጠር በኩባያ ስር አስቀምጠው የሚቆምሩት ወመኔዎች(ዱርዬዎች)  ትዝ ይሉኛል።

በሚያደርጉት የተንኮል ዘዴ ቀልቡ የማይሳብ የለም።ዕቃ ለመግዛት ፍራንኩን ቋጥሮ ወደ መርካቶ ደፋ ቀና የሚለው የዋህ ገበያተኛ በወመኔዎቹ ግፊና  ሰበካ ተጠልፎ የዘረፋው ሰለባ ይሆናል። ማጭበርበሩ እንዲህ ነው፤የቡድኑ መሪ  ሁለት ኩባያዎችን በመሬት ላይ ባነጠፈው እራፊ ሰሌን ወይም ካርቶን ላይ ባፋቸው ደፍቶ ያስቀምጣል።ከተቀመጡት ኩባያዎች መሃል አንዱን ያነሳና ሰው እያየው ጠጠሩን አስቀምጦ መልሶ ኩባያውን ይጭንበታል።

በዚህ መካከል ሌላው/ሌሎቹ ተባባሪዎቹ የሆነ ያልሆነውን እየዘላበዱ፣ተጨዋች  መስለው የተመልካቹን ትኩረት ይቀይሩታል፤በዚህ ግርግር “አጫዋቹ” ወመኔ ጠጠሯን ከነበረችበት ኩባያ ስር ወደሌላዋ ኩባያ ስር ያስቀምጣታል።ሚስጥሩን የሚያውቁት ተባሪዎቹ እዚህ ስር ነው 1 እዚያ ስር ነው እያሉ በመወራረድና በመፎካከር ገንዘብ ይመድባሉ።ሌላውም መንገደኛ አገኘለሁ ብሎ ያለችውን ፍራንክ ይመድባል።

የምደባው ተሳትፎ እንዳበቃ ውጤቱን ይፋ ለማድረግ ኩባያው ሲነሳ፣አሸናፊዎቹ የወመኔው ቡድን አባላት ይሆናሉ።በዚህ መልኩ አላፊ አግዳሚው፣ተንኮል የማያስበው  መንገደኛ አተርፍ ባይ አጉዳይ ሆኖ  ያሰበውን ሳይገዛ ባዶ እጁን እየተበሳጨ ወደቤቱ ይመለሳል።

ይህንኑ ቦቼ-ቦቼ፣ወጣ-ገባ መሳይ ቁማር ላለፉት አርባ ዓመታት በኢትዮጵያ በአገራችን ሥልጣን በያዙት መንግሥታትና አሁንም በትግል ላይ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶችም ሲጠቀሙበት ለመታዘብ ችለናል።

በደርግ ጊዜ “የእናት አገር ጥሪ” በሚለው ቅስቀሳ ወቅት በየቀበሌው ሰፊ ዝግጅት ተደርጎ በአዳራሽና በድንኳን አንድ የባህል ዕቃ ወይም የኢትዮጵያ ካርታ ለጨረታ ይቀርባል፣በዚያ ጨረታ ላይ  የቀበሌው ሠራተኞችና አንዳንድ ነዋሪዎች እንዲሳተፉ

ትዕዛዝ ይሰጣቸዋል።ጨረታው በተወሰነ ገንዘብ መነሻ ይጀመርና በቅድሚያ ትእዛዝ የተሰጣቸው እየተጫረቱ ሞቅ ሞቅ አድርገው የዕቃውን ዋጋ ጣራ ያደርሱታል።

በዝግጅቱ ላይ እንዲገኝ የተገደደው የቀበሌ ኗሪ በአናርኪስትነት ላለመጠርጠር ከፍርሃት ወይም ለአገሩ ካለው ፍቅር በመነሳት ከማን አንሼ ውድድር ውስጥ ይገባና ለቀረበው ዕቃ የማይገባውን የጨረታ ዋጋ ከፍሎ ለመውሰድ ይገደዳል።የእለቱ አሸናፊ ! አገር ወዳድ! ተብሎ በጭብጨባ ስሙ እየተጠራ በሙገሳ ተጀጅሎ ይመለሳል።

በአሁኑ የህወሃት/ኢሕአዴግ ዘመንም የተወረሱ ዕቃዎች ለሽያጭ በጨረታ መልክ ይቀርባሉ፤ለመወዳደር ምዝገባ ብቻ የማይመለስ ብዙ ሽህ ብር ይጠየቃል፤ተጫርጬ አገኛለሁ የሚለው ተስፈኛ የተጠየቀውን ከፍሎ ለጨረታው ይሰለፋል።የሚፈለገው ያህል ገንዘብ ከተሰበሰበ በኋላ ጨረታው ሳይካሄድ ይሰረዛል ወይም ውስጥ ለውስጥ የሚፈልጉት ሰው እንዲያሸንፍ ይደረጋል።

በሌላም መልክ በልዩ ልዩ አገራዊ ስሜትን በሚቀሰቅሱ የልማት ዕቅዶች ስም በተዘጋጁ የእርዳታና የቦንድ ሽያጭ አገር ወዳዱ በተመሳሳይ መንገድ እየተበዘበዘ ነው።በአገር ቤትና በውጭ አገር በሚደረጉት ዝግጅቶች የመንግሥት ደጋፊዎች በቅድሚያ ገንዘብ በመውሰድ ወይም በመጨረሻው የሚመለስላቸውን ገንዘብ በማበርከት የሌላውን ልብ ይሰቅሉታል፣እርዳታ እንዲሰጥ ወይም ቦንድ እንዲገዛ ያማልሉታል።

አንዳንዱም ሌላውን እያዩ ከማን አንሼ ውድድር ውስጥ ይገባና ለዝርፊያው የተመቼ፣ቢያልቡት የማይነጥፍ ላሜ ቦራ ይሆናል። አገር ወዳዱ ለአገሩ እድገትና ልማት አበረከትኩ ብሎ የሚያስበው ገንዘብ በባለሥልጣናቱ የግል የባንክ ቁጥር እንደሚገባ አይገነዘብም።ቢነግሩትም አይሰማም።

እንዲሁ እየተሞኘ ጥሪውን በመቀበል ካገር አገር በመኳተን ላይ ነው።የኋላ ኋላ ሚስጥሩ ሲገለጽለት ሊቆጨው ይችላል፤ያ ከመሆኑ በፊት ግን አሁን መንግሥት የሚያካሂደውን ዘረፋና አገር በታታኝ እርምጃ ቢያጤነውና ቢቃወመው ለአገሩ የበለጠ እርዳታ እንደሰጠ ይቆጠርለት ነበር።

በፖለቲካ ድርጅትም ዙሪያ ተመሳሳይ "ወጣ-ገባ! ቦቼ-ቦቼ" የነዛን በመርካቶ አካባቢ በመንገድ ዳርና በድልድይ ሥር ተኮልኩለው ካርቶን አንጥፈው የሚያጭበረብሩ ወመኔዎች ዘረፋ በሚመስል መልኩ ማጭበርበር ሲካሄድ፣ እንደ ደርግና ህወሃትም ጆሮ በሚያደነቁር ዲስኩርና ሙዚቃ የታጀበ ዘረፋ ሲፈጸም ታዝበናል(ለመሆኑ እነዛው የመርካቶዎቹ ወጣ ገባ፣ቦልቼ! ቦልቼ አጭበርባሪዎች ይሆኑ ይሆን በየጊዜው ሥልጣን ላይ የተቀመጡትና አሁን ድረስ በየፖለቲካው ድርጅት ውስጥ ገብተው የሚያምሱት?) እንደቀበሌውና እንደ ህወሃት አባላቱ የተቃዋሚ ድርጅቱ አባላትና ደጋፊዎችም ከድርጅት ካዝና ወጥቶ የተሰጣቸውን ገንዘብ መድበው ለጨረታ በቀረበው ዕቃ ላይ ሲረባረቡ፣እርዳታ በመስጠቱ ላይ ግንባር ቀደም እየሆኑ አቅማቸው የማይፈቅደውን ገንዘብ ሲቸሩ፣ሌላው የዋህ አገር ወዳድ እውነት መስሎት ያለውን ሁሉ ሲለግስና ለጨረታው ሲመድብ ማየት የተለመደ ቲያትር ሆኗል።

የፖለቲካ ድርጅቶች የሚያካሂዱትን ጨረታ(ቁማር) ከሌሎቹ ለወጥ የሚያደርገው ነገር የዕቃው መነሻ ከተወሰነ በኋላ በዛ ዋጋ እገዛለሁ የሚለው ገንዘቡን ይሰጣል፤ሌላው አብልጦ ገንዘብ ይጥላል፤እንዲህ እያለ ይሄድ ይሄድና መጨረሻ ላይ በድርጅቱ ገንዘብ የሚፎካከረው አሸነፈ ተብሎ ይሰጠዋል።ሌላው በውድድሩ የጣለው ገንዘብ አይመለስለትም፤ለድርጅቱ ገቢ ሆኖ ይቀራል።ያ የፈረደበት ዕቃ በሌላ ቦታ፣ አገር ላገር እየዞረ ለሚካሄደው የማጭበርበር ተግባር ዳግመኛ ለጨረታ ይቀርባል።በዚህ መልክ ብዙሃኑ በአገር ፍቅር ሰበብ፣በትግል ስም ይበዘበዛል።

በዚህ አይነቱ የማጭበርበር ተግባር ላይ የተሰለፉት መንግሥታትም ሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች መጨረሻቸው አያምርም።ደርግ ወደቀ፣ህወሃት/ኢሕአዴግም እየተንገዳገደ ነው፤ይወድቃል።በማጭበርበር እንጠቀማለን፣ሥልጣን እንይዛለን ብለው የሚያስቡ የፖለቲካ ፓርቲዎችም፣አይሳካላቸውም፤የጊዜ ጉዳይ ነው ይጋለጣሉ።አሁንም እየተጋለጡ ነው።

አንድ ጊዜ መሞኘት ከቅንነት የመነጨ ሊሆን ይችላል፤ ደጋግሞ መሞኘት ግን ጅልነት ነው። ለአገሩ የረዳ መስሎት ገንዘቡን በተለያየ መልክ የሚዘረፈው አገር ወዳድ አድራጎቱን ሊያጤነው ይገባል።በድራማና በአሸሼ ገዳሜ ጫጫታ መታለል አይኖርበትም። የመንግሥትንም ሆነ የተቃዋሚውን አካሄዱን መከታተል ለምን አይነት ለውጥና ስርአት የቆመ መሆኑን ለማወቅ ይረዳል።የኋላ ኋላም “አሶስጄ መጣሁ አሶስጄ” ከሚለው እንጉርጉሮ ያድናል።

“ከወጣ-ገባ፣ቦልቼ-ቦልቼ” ቁማርተኞች፣የመንግሥትና የፓለቲካ ቡድኖች እንጠንቀቅ!!

አገሬ አዲስ

**http://www.ethiopanorama.com**